የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፸፮
አዲስ አበባ መስከረም ፴ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No.76
ADDIS ABABA 10th October, 2014

**ማውጫ**

ደንብ ቁጥር ፫፻፳፪/፪ሺ፯ ዓ.ም

የአርሲ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ……………………………………ገጽ ፯ሺ፮፻፷፯

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፳፪/፪ሺ፯**

**የአርሲ ዩኒቨርሲቲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ (በአዋጅ ቁጥር ፰፻፫/፪ሺ፮ እንደተሻሻለው) አንቀጽ ፭ እና አንቀጽ ፴፭ እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ አንቀጽ ፭(፩) መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የአርሲ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፳፪/፪ሺ፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **መቋቋም**

፩/ የአርሲ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡

**CNTENTS**

Regulation No. 322/2014

Arsi University Establishment Council of Ministers Regulation…………………………………………Page 7667

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 322/2014**

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF ARSI UNIVERSITY**

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 and Article 35 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No.691/2010 (as amended by Proclamation No. 803/2013) and Article 5(1) of the Higher Education Proclamation No. 650/2009.

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as the "Arsi University Establishment Council of Ministers Regulation No. 322/2014".

2. **Establishment**

1/ Arsi University (hereinafter the "University") is hereby established as an autonomous higher education public institution having its own legal personality.

2/ The University shall be accountable to the Ministry of Education.

፫/ ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲ ዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፲/፪ሺ፫ መሠረት ይተዳደራል፡፡

3/ The University shall be governed by the Higher Education Proclamation No. 650/2009 and the Federal Universities Council of Ministers Regulation No. 210/2011.

**፫. ዋና ግቢ**

የዩኒቨርሲቲው ዋና ግቢ በአሰላ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

**3. Main Campus**

The University shall have its main campus at Asela town and may establish elsewhere other academic units and centers of research and community services.

**፬. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከመስከረም ፳፫ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**4. Effective Date**

This Regulation shall enter into force as of the 3rd day of October, 2014.

**አዲስ አበባ መስከረም ፴ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም**

**Done at Addis Ababa, this 10th day of October, 2014.**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት